# በአቅም ግንባታ ሴክተር
# የለውጥ ፕሮግራሞች የፕሮጀክት ጥናትና
# ትግበራ ዋና የስራ ሂደት
# የ2002 በጀት ዓመት
# ጠቋሚ ዕቅድ

ግንቦት 2001

ሀዋሳ

# ማ ው ጫ


ገጽ

1 መ□ቢጸ ........................................................................................ 1

2 ያለፈው በጀት አመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ.................. 2-5

3 □ላማ.............................................................................................. 6

4 ቁልፍ ፣□በይትና ንዑሳን የትኩረት መስኮች....................................... 6-11

5 ዓመታዊ ግቦች የውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች........................ 12-17

6 የሚጠበቁ ውጤቶች ................................................................. 15-23

7 የሰው ሀይልና የበጀት ዕቅድ ................................................................

8 አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች.......................................................... 20-21

8.1 አዎንታዊ ታሳቢዎች....................................................... 20

8.2 አሉታዊ ታሳቢዎች............................................................ 21

9 የክትትል፣ ግምገማ፣ሪፖርትና ግብረመልስ ስርዓት............................ 21

9.1 የክትትልና ሪፖርት ስርዓት ................................................ 24

9.2 የግምገማ ስርዓት ............................................................... 26

10 የአፈጻጸም መርሃ ግብር……………………………………………………

10.1 የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም…………………………….. 27-31

10.2 የወረዳ አቅም ግንባታ ኘሮግራም……………………………… 32-37

10.3 የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም……………………………… 38-41

10.4 የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም……………………….. 42-46

## 1. መግቢያ

በክልላችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ከልማቱም ህዝቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ እንዲቻል መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ወሳኝ ነው። በዚህ መሰረት ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም የመገንባት ሥራ ትኩረት በመስጠት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ /BPR / በክልሉ ሙሉ በሙሉ በመተግበር ተቋማዊ ለውጥ /Organazational Transformation / የማምጣት ጉዳይ ትኩረት ይደረግበታል። በመሆኑም የክልላችን ሕዝብ ከሚገኝበት ኋላ ቀርነትና ድህነት እንዲላቀቅ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገብናቸውን የልማት ውጤቶች ዘላቂ እንዲሆኑና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በክልሉ የሚታዩ የማስፈጸም አቅም ችግሮችን ለፈታ □ሚችል የዳበረ ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባት ይጠይቃል።

በየደረጃው የሚታዩትን □ማስ□□ም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ በመፍታት ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከር፣የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ፈጥኖ መፍታት የሚያስችል ስልት በመቀየስ በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግና አጠቃላይ የሪፎርም ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ በማስተገብር በመንግስት ተቋማት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዲቻል መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ማድረግና የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት መዘርጋት ቁልፍ የትኩረት መስክ ይሆናል።

በአጠቃላይ የ2002 በጀት ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ በዋናነት የዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስርዓት ማስፈን፤ በመንግሥት ተቋማት ቀልጣፋና ውጤታማ አሠራርን መዘርጋት መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ መሠረት □አቅም ግንባ□ ሴ□ተር ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸውን ተግባራትንና ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም የተገኙ ውጤቶች፤ አገራዊ የትኩረት አቀጣጫዎችንና የሴክተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች በዋና ግብዓትነት በመውሰድ የ 2002 በጀት ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

## 2. ያለፈው በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም አጭር ግምገማ

በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በ2001 በጀት ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ በታቀደው መሰረት በዋነኛነት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የተከናወነ ተግባር ሲሆን በመጀመሪያ ዙር የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በታቀፉ 7 ሴክተር መ/ቤቶች 34 የስራ ሂደቶች ተጠንተው በ3 ዞኖች 3ወረዳዎችና 5 ከተማ አስተዳደሮች የሙከራ ትግበራ አድርገው ወደ ሙሉ ትግበራ ተሸጋግረዋል ፡፡ በሙከራ ትግበራ ወቅት በክልሉ የቴክኒክ አማካሪ ቲም አማካይነት የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

ሰባቱን ሴክተር መ/ቤቶች ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት ለ2,630 ለሚሆኑ ሰልጣኞች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት በተዋረድ ለ24,370 ፈጻሚዎች በተደለደሉበት የስራ ሂደት ጥናት ሰነድ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

በሁለተኛ ዙር የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በሴክተር መ/ቤቶች በማካሄድ 60 የስራ ሂደቶች ጥናት አጠናቅቀው በተመረጡ 4 ዞኖች 4 ወረዳዎችና 4 የከተማ አስተዳደሮች ወደ ሙከራ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት የሙከራ ትግበራ እንዲገቡ ለማስቻል የእቅድ ቢጋር በማዘጋጀት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ ሀሳብ ላይ ለ250 የበላይ ሀላፊዎች የሴክተር መ/ቤቶች ኮር ቲም አባላት ለ400 የሪኢንጂነሪንግ ቲም አባላት 46 የሁሉም ዞንና ልዩ ወረዳ ሀላፊዎችና ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ☞ የሁለተኛ ዙር የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ሲካሄድ ሴክተሮች በራሳቸው ከሚያደርጉት ክትትል ድጋፍ በተጨማሪ የሥራ ሂደቶችን በክላስተር በመከፋፈል በእያንዳንዱ የጥናት ደረጃ የቴክኒክ ድጋፍ የተሰጠ ሲሆን ሁሉም የሥራ ሂደቶች በጋራ በቴክኒካል ቲም አባላት ለአንድ የጥናት የደረጃ ከ15 ቀናት ላላነሰ

ጊዜ የቴክኒክ ድጋፍ በክልል ስትሪንግ ኮሚቴም በመስጠት ለሚጥለው ደረጃ እንዲያልፉ ተደርገዋል፡፡

- ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት በክልሉ ስትሪንግ ኮሚቴና ቴክኒካል ቲም ስትራቴጁና ደንብ በማውጣት ለሥራ ሂደቶች ተሰራጭቷል፡፡
- 300 ለሚሆኑ የዞን የልዩ ወረዳ ገጠር ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር አቅም ግንባታ ኃላፊዎች በለውጥ ኘሮግራሞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን የሰለጠኑ ኃላፊዎችም የራሳቸውን ሴክተር መ/ቤቶችንና ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ሥልጠና ሰጥተዋል

ለዞን፣ለልዩ ወረዳና ለወረዳ አቅም ግንባታ ሴክተር ሃላፊዎች፣ ለም/ቤት አባላት፣ ለመንግስት ሰራተኞችና ለቀበሌ ሥራ አስኪያጆች በሲ/ሰ/ማ/ፐ/ በተለያዩ ርዕሶች ለ 1063 አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

***<u>በወረዳ አቅም ግንባታ</u>*** ያልተማከለ አስተዳደርና በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የ 2001 በጀት አመት የአፈጻጸም ግምገማ በአጭሩ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት በፌዴራል ደረጃ የተካሔደው የእንስፔክሽን ውጤት መሰረት በማድረግ መልካም አስተዳደርን ፓኬጅ በተፋጠነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረ የእንስፔክሽን ክትትልና ግምገማ ስርዓትን በመዘርጋትና የሙያ ድጋፍ በመሥጠት የ2001 የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅዶቻችንን ለማሣካት ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የምርጥ ተሞክሮ መቀመሪያ ቢጋር ከክልል እስከ ወረዳ አስተባባሪ እና ቴክኒካል ኮሚቴ አደረጃጀትን በሚያሳይ መልኩ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች አቅም ግንባታ ተቋማ ሃላፊዎች ጋር በመወያየት በዚህ መነሻ የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ሥራ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች አሰራርን በተጠናከረ መልኩ ለመደገፍ በታቀደው መሰረት ከ124 ወረዳዎችና ከአስራ ሦስት ዞኖች ለተወጣጡ 137 የሰው ሃብት ልማት ባለሙያዎች የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን እንዲያሰለጥኑ ለ10 ቀናት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በገጠር ወረዳ ያልተማከለ አስተዳደርን ዉጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የተቀናጀ የወረዳ እና የቀበሌ ዕቅድ አዘገጃጀት ሥርዓትን ለመዘርጋት

በታቀደው መሰረት የዝግጅቱ አካል የሆነውን የመነሻ ሃሳብ / concept paper / የማዘጋጀት ሥራ ተሰርቷል።

ኅብረተሰቡን በግልና በጋራ ሥራ የማሣተፍና አሣምኖ ማሠራትን ባህል ለማዳበርና ሞዴል የመጠቀም ስርዓትን ለመዘረጋት በታቀደው መሰረት በክልሉ ወረዳና ቀበሌ ደረጃ በርካታ ሞዴል ቀበሌዎችን፣መንደሮችንና ግለሰቦችን ለማፍራት በርካታ ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም ስፊውን አርሶ አደር ለላቀ ልማት ለማነሳሳት የልማት አርበኛ አርሶ አደሮችን፣ የቀበሌ አስተዳዳሪዎች፣የግብርና ልማት ባለሙያዎችና የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በመለየት የማበረታቻ ሽልማት የመስጠት ሥራዎች በስፋት እየተከናወነ ይገኛል። ይሁን እንጂ በዚህ ዙሪያ በርካታ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዩች ተለይተዋል።

የአርብቶ አደር አካባቢ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ከ3 የአርብቶ አደር ዞኖች (ደ/ኦሞ፣ቤንችማጂና ከፋ) ግብዓት የማሰባሰብ ሥራ በማከናወን ፓኬጁን ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አስማምቶ በማዘጋጀትና ለክልሉ ካቤኔ በማፀደቅ የስትሪንግና ቴክኒካል ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ተሟላ ትግበራ ተገብቷል።

***<u>በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም</u>*** ተግባራዊ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ ከተቀመጡ ግቦች የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

ለክልሉ ፍትህ ስርዓት ስኬታማነት ተቋማዊ አቅምን ለመፍጠር በታቀደዉ መሰረት አንድ የፍትህ አካላት ባላሙያዎች የህግ ምርምር ማሰልጠኛ ማዕከል ተቋም የዉስጥ ቁሳቁስን እንድሟላ ጥረት ተደርጓል 400 አዲስ የወረዳ ዳኞችና አቃቢያን ህግን ለማሰልጠን ታቅዶ 150 ዕጩዎች ተመልምለዉ ሥልጠና እየተሰጣቸዉ ሲሆን በዚህ ዓመት መጨረሻ ላይ ተመርቀዉ ስራ እንዲጀምሩ ይደረጋል። ሆኖም ግን በዓመቱ ለማሰልጠን ከታቀደዉ 38% ብቻ ተግበራዊ የተደረገ ሲሆን 62% በተለያዩ ምክንያት ለማሰልጠን አልተቻለም ። የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ፅንሰ ሃሰብ በሁሉም የክልል ቀበሌ አደራጅቶ ሥራዉን ለማሠራት የታቀደ ሲሆን በተወሰነ ወረዳ ያልተደረጃ ቢሆንም በሌሎች በተለያዩ ወረዳዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግን አደረጃጀት በማጠናከር የአካባቢያቸዉን ሰለምና ፀጥታ ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ መዝገብ አዘጋጅተዉ በየተራ የአካባቢያቸዉን ደኅንነት እንዲጠበቅ አድርጓል ተጨማሪ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ፅንሰ ሃሰብ አተገባበር ላይ ለ255 ፖሊስ አባላት ለአንድ ዓመት ሥልጠና እንዲሰጣቸዉ ተደርጓል።

ለ23ቱ የማረሚያ ተቋማት ለ69 ከፍተኛ የፖሊስ መኮንኖች አቅም ለመገንባት ህግ ታራሚዎችን ሰብአዊ መብት አጠባበቅና አያያዝ የተሻለ ለማድረግ በመልካም አስተዳደር ለአምስት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪ ለ132 የማረሚያ ቤት የጥበቃ ፖሊስ አባለት የአቅም ግንባታ ሥልጠና በታራሚዎች አያያዝ ላይ በክልሉ ፖሊስ ኮሌጅ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተወሰኑ ማረሚያ ቤቶች አሥር ክሊኒኮች ተቋቁመዉ ባላሙያ ተመድቦላቸዋል፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ለህክምና ይወጣ የነበረዉ ከፍተኛ ወጪ በ50% ሊቀንስ ችሏል፡፡ ክሊኒክ የሌላቸዉ ማረሚያ ተቋማት በአቅራቢያ በሚገኙ የጤና ተቋማት ህክምና እያገኙ ሲሆን ከአቅም በላይ የሆኑት ወደ ሪፌራል ሆስፒታል እየተወሰዱ ህክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡ የክልሉን አዋጆችና ደንቦች አሳትሞ ለማሰራጨት በታቀደዉ መሠረት 81 አዋጆች በ3366 ኮፒ በሦስት ጥራዝ እንዲታተም ተደርጎ ለሁሉም ለሚመለከታቸዉ አካላት እንዲሰራጭ ተደርጓል ፡፡

ከአርብቶ አዳሩ አካባቢ 100 ተማሪዎች ተመልምለዉ የህግ ትምህርት በዲፕሎማ እንዲማሩ ታቅዶ የነበረዉ አሳልጠኝ ተቋማት በወጣዉ ጨረታ በወቅቱ ባለማግኘታችን እስከ 3ኛዉ ሩብ ዓመት ሳይከናወን ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ሩብ ዓመት በወጣዉ ጨረታ አሸናፊ ተለይቶ በመታወቁ በቅርቡ ስምምነት ከዛየን ኮሌጅ ጋር ከተደረሰ በኃላ ትምህርታቸዉን እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ አንጻር በተመራጩ የሥራ ሂደት ዓይነቶች ማለትም የህብረተሰቡን ሰለምና ፀጥታ ለመጠበቅ በወንጀል መካለከል የሥራ ሂደት በሁሉም ዞን፣ ልዩ ወረዳና ወረዳ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ አደረጃጀት በማጠናከር በየአካባቢ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ሰለም ጠንቅ የሆኑ ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ በማረምና ማነፅ የሥራ ሂደት በፍርድ የታሰሩ እስረኞች ሰብአዊና መሠረታዊ ነፃነቶች የሚጠባቁበት ሁኔታ በማደሪያ ቤት ፣ በምግብና በህክምና እንዲመቻች ተደርጓል እስረኞች በእስር በሚቆዩበት ወቅት የተለያዩ የቀለምና ሙያ ትምህርት ቀስመዉ እንዲወጡ ተደርጓል ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ዘመዶቻቸዉ ጋር በፕሮግራም እንዲገናኙ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል አቤቱታ የመመርመርና ወሰኔ የመሰጠት ዋና የሥራ ሂደት በተገልጋዩ ፍላጎት ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል ተያያዥነት የሏቸዉን ተግበራት በማሳብሰብ ያለዉጤት እንደይበጣጠሱ በማድረግ

ለተገልጋዩ ፍላጎት በአፈጠኝ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ በግብ ስኬቶች ላይ እንዲያተኩር ተደርጎ ተደረጅቷል በፖሊስ በአቃቤ ህግና በፍርድ ቤት ተበጣጥሶ ይሰራ የነበረዉን በማቀናጀት ዉጤት በሚየመጠ መልኩ በአንድነት ለማስከሄድ ተደረጅቷል

*<u>የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም</u>* የዕቅድ አፈፃፀም ሲታይ የተሻለ የሥራ አፈፃፀም የታየበት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በኘሮግራሙ ከተካተቱ ኘሮግራሞች አብዛኛዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተከናውነዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ሲታይ በኘሮግራሙ የተቀመጠውን ለማሣካት በሚደረገው ጥረት ያጋጠሙ ችግሮች አልነበሩም ማለት አይቻልም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ በምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም በማስፈፀም ስልት በፈፃሚዎችና በአስፈፃሚዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር አለመቻሉ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የግንኙነትና የቅንጅት ችግር መኖሩ፣ በኘሮግራሙ አፈፃፀም ላይ ብቃት ያለው ድጋፍ መስጠትና ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረመልስ መስጠት አለመቻል፡፡ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በዕቅድ አፈፃፀማቸው አካትተው እንደዋና ተግባራቸው አድርገው አለማየትን የመሣሰሉ ነበሩ፡፡

## 3/ አጠቃላይ ዓላማ

የመንግስት ተቋማትን የማስፈጸም የአቅም በመገንባት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ነው፡፡

## 4/ የሂደቱ ቁልፍና አበይት የትኩረት መስኮች

### I. ሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም / CSRP /

**ቁልፍ የትኩረት መስክ**

የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ማድረግና ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ስርዓት በመዘርጋት ተቋማዊ ለውጥ/Organizational Transformation/ መምጣቱን ማረጋገጥ ነው፡፡

**አላማ**

የመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የመንግስት ፖሊሲዎች ፕሮግራሞችና ስትራጂዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ

ለውጥ ማምጣት ነው፡፡

**ግቦች**

- የመሰረታዊ የሥራ ሂደት /BPR/ አተገባበርን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተፈጠረ የአሠራር ሥርዓት

- በሁሉም መንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ ሥርዓት

- የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን የተሟላ ለማድረግ በፌደራል ተጠንተው የሚወርዱ የጥናት ውጤቶችን ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ በማዘጋጀት የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት

## አበይት የትኩረት መስክ

ለጋምቤላ ክልል በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥና በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ስርዓት ዝርጋታ የስልጠና ድጋፍ በመስጠት ማብቃት

**ግብ**

- ከጋምቤላ ክልል ጋር በተገባው ስምምነት መሰረት በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተሰጠ ድጋፍና የምክር አገልግሎት
- ለጋምቤላ ክልል በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ምዘና የተሰጠ ድጋፍና የምክር አገልግሎት
- መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋፋት

## II. የወረዳ ያልተማከለ አቅም ግንባታ ኘሮግራምና የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ/DLDP&GGP/

**ቁልፍ የትኩረት መስክ**

የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጉ ሥርዓቶችን እንደ ሥርዓት አጠናክሮ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግና ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋፋት በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ነው፡፡

**ግቦች**

- በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት፣
- በሁሉም የክልሉ የቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር

እንዲመራ ማድረግና አሣምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋፋት፣

- በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት
- በሁሉም የአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደርጎ የተቀረፀውን የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መተግበር

**ዓበይት የትኩረት መስክ**

የወረዳና የቀበሌ ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከር ልዩ ልዩ ተቋሚዊ ጥናቶችን በማካሄድ የወረዳና የቀበሌ ተቋማት አፈጻጸምን መደገፍ

- በየደረጃ ባሉ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት ለመተግበር የተጠናቀቁ የጥናት ውጤቶችን ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በመቃኘት ተግባራዊ ማድረግ

- በወረዳና በቀበሌ ደረጃ  የህዝብ ፍላጎትና ቅሬታ የሚታወቅበት ጥናት በማካሄድ የመልካም አስተዳደር እመርታን በቀጣይነት ማረጋገጥ

## III. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም/JSRP/

**ቁልፍ የትኩረት መስክ**

የክልሉን የፍትህ ሥርዓት ለማሻሻልና ከመሠረቱ ለመለወጥ የተወጠኑ ሥራዎችን በማጠናከር የፍትህ ስርዓቱን ተደራሽነት፣ቀልጣፋነት፣ ፍትሃዊነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ነው፡፡

**ዓ ላ ማ**

ኀ/ተሰቡ ያለምንም ውጣውረድና አድልዎ ነፃ በሆነ መልኩ ጥራት ያለው ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት እንዲያገኝ ማስቻል፣

**ግቦች**

- በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትን ስልጠናና የህግ ምርምር ማዕከል ማብቃትና ተkሙን በማቴሪያል መደገፍ ፣

- የኅብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ሥርዓት፣
- ህብረተሰቡ የፍትህ ሥርዓቱን የራሱ መሆኑን ተገንዝቦ አጥጋቢ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርግበት የአሠራር ሥርዓት
- በክልሉ በሁሉም ቀበሌያት ከመደበኛ ፍርድ ሥርዓት ውጭ የተዘረጋ አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ አሰራር ስርዓት፣

## IV. የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም/ ECBP /

**ቁልፍ የትኩረት መስክ**

የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልክ ከባለድርሻ አከላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረግ፣

**ዓ ላ ማ**

የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ፈጣንና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተፈጻሚ እንዲሆን ማስቻልና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ ፣

**ግቦች**

- ❖ አሠራራቸው የተለወጠና በአዲሱ የአሠለጣጠን ዘዴ ሥልጠና የጀመሩ የመንግስትና የግል ቴ/ሙ/ተቋማት
- ❖ አሠራራቸውን በማሻሻል ከኢንዱስትሪው ጋር የተቀናጀ አሠራርን የጀመሩ ዩኒቨርሲቲዎች
- ❖ አቅማቸውን አጎልብተው ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አሠራር የዘረጉ ተቋማት
- ❖ በእሴት ሰንሰለት አሠራር ሥርዓት መሠረት ሥራቸውን የጀመሩ የግል ሴክተሮች
- ❖ በመንገድ ልማቱ ዘርፍ የንጣፍ ድንጋይ ሥራን የተገበሩ የሪፎርም ከተሞች
- ❖ የተደራጁና ድጋፍ የተደረገላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት

**ዓበይት የትኩረት መስኮች**

የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም በመንግሥትና በግል ተቋማት አዲስ

አሠራርና አመለካከትን በማስረፅ ሂደቱን በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ክትትልና ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት

## ግቦች

- የግል የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት ተፈላጊ የሙያ መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ በሁሉም በመንግሥትና በግል ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት የሚያስችል የተፈጠረ የሰው ኃይል

- የእሴት ሠንሠለት (Value Chain) አሠራርን በማስተሳሰር በሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ዘንድ የተተከለ አሰራር

- በቴ/ሙ/ተቋማት የተደረገ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሽግግር አሰራር

## 3. የዓመታዊ ግቦች ውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሲቪል ሰርቪስ ኘሮግራም ቁልፍ የትኩረት መስክ | | | |
| 1 | የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ማድረግና ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ስርዓት በመዘርጋት ተቋማዊ ለውጥ/Organizational Transformation/ መምጣቱን ማረጋገጥ ነው | | | |
| 1.1 | በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት /BPR/ አተገባበርን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ | በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በከፍተኛ ጥረት ተደርሽ ግቦችን ያሳኩ መ/ቤቶች ብዛት | - ሥር ነቀል የአሠራር ለውጥ<br>- ቀልጣፋ የአገልግሎትአሰጣጥ<br>- የተገልጋዮች እርካታ | የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 1.2 | በሁሉም መንግስት ተቋማት ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ /BSC/ ተግባሪዊ ለማድረግ የተዘረጋ | - የ/BSC/ሥርዓትን የተገበሩ ሴ/መ/ቤቶች ብዛት | ሥር ነቀል የአሠራር ለውጥ ቀልጣፋ የአገልገሎት አሰጣጥ የተገለጋዮች እርካታ | የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 1.3 | የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግበራን የተሟላ ለማድረግ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተዘጋጁ የጥናት ውጤቶች | -ከኃላፊነት የሚነሱ ተሿሚዎች ለማስጠበቅ የተዘረጋ ሥርዓት<br>▪በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት<br>▪የማወዳደሪያ ዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት<br>▪የሲሰማፕ ስኬትና ጉድለቶች መለያና ማጠናከሪያ በገለልተኛ አካልት የተጠና ጥናት | | |
| 2 | ለጋምቤላ ክልል በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥና በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ስርዓት ዝርጋት የስልጠና | | | |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| | ድጋፍ በመስጠት ማብቃት | | | |
| 2.1 | ከጋምቤላ ክልል ጋር በተገባው ስምምነት መሰረት በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የተሰጠ ድጋፍና የምክር አገልግሎት | በአገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍ የተደረገላቸው የመንግስት ተቋማት ብዛት እና የሰለጠኑ ሰዎች ብዛት | ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥናየተገልጋዮች እርካታ<br><br>ውጤታማ የዕቅድ አፈጻጸም | የተፋጠነ ማህ/ኢኮ/ ልማት |
| 2.2 | በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ምዘና የተሰጠ ድጋፍና የምክር አገልግሎት | | | |
| II. | **የወአግፕ ቁልፍ የትኩረት መስክ** | | - | |
| 2 | የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጉ ሥርዓቶችን እንደ ሥርዓት አጠናክሮ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግና ምርጥ ስኬቶቻችንን በማስፋፋት በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ነው | | | |
| 2.1 | በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት | ❖ ኢንስፔክሽን ቡድን የተቋቋመባቸው ወረዳና ቀበሌዎች ብዛት<br>❖ ለኢንስፔክሽን አሠራር ማስፈፀሚያ የተዘጋጀ ሠነድ<br>❖ በኢንስፔክሽን ላይ ሥልጠና የወሰዱ አካላት ብዛት<br>❖ የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣቸው ወረዳና ቀበሌ ብዛት<br>❖ የአሠራሩን ለማጠናከር የተሠጠ ድጋፍና ክትትል | • የእንስፔክሽን ሥራውን ተግባራዊ ያደረጉ የእንስፔክሽን ቡድኖች ብዛት<br>• በስልጠናው የረኩ የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ብዛት<br>• በወረዳና ቀበሌ መካከል የተፈጠረ የጠበቀ ግንኙነት (communication & cooperation improved)<br>• ተቋማዊ አሰራራቸውን ያስተካከሉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ብዛት | • በግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራር ላይ ለውጥ ያመጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ብዛት |
| 2.2 | በሁሉም የክልሉ የቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ | • ሞዴል ለመምረጥ የሚያስችል | • በማህበረሰብ ውስጥ የተፈጠረ | • የዲሞክራሲያዊ አሠራር |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| | አደር እንዲመራ ማድረግና አሣምኖ ማሠራትን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋፋት | የተፈጠረ የተቀናጀ አሠራር<br>• በወልና ግል ሥራ ላይ በተገቢው የህ/ሰብ ተሣትፎን ለማረጋገጥ የተፈጠረ አሠራር<br>• ለምርጥ ተሞክሮ የተዘጋጀ ሰነድ | የልማት ተነሣሽነት<br>• በሞዳሉ አመራረጥ ላይ የህብረተሰቡ ዕርካታ<br>• የህ/ሰብ ተሣትፎ መጠን | መጎልበት<br>• በገጠር ወረዳና ቀበሌ የልማታዊ ፓለቲካል ኢኮኖሚ አስተሳሰብ መዳበር |
| 2.3 | በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት | • ስልጠና የተሰጣቸው ሥራ አስኪያጅ ብዛት<br>• ተቋማዊ አሰራር የዘረጉ ቀበሌያት ብዛት | • በቀበሌው ልማት ውሰጥ የተፈጠረ ተነሣሽነት<br>• በቀበሌው አሰራር የህብረተሰቡ ዕርካታና የህ/ሰብ ተሣትፎ መጠን | • በግልፅነትና ተጠያቂነት አሠራር ላይ ለውጥ ያመጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ብዛት |
| 2.4 | በሁሉም የአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደርጎ የተቀረፀውን የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መተግበር | • ለአርብቶ አደር አካባቢ በመልካም አስተዳደር ላይ የሠለጠኑ አካላት ብዛት<br>• በሥርዓቱ አተገባበር ላይ የተሠጠ ድጋፍና ክትትል<br>• የተዘጋጁ ልዩ ልዩ መመሪያዎች | • በስልጠናው የረኩ ሠልጣኞች ብዛት<br>• ፓኬጁ ተግባራዊ የሆነበት የአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ብዛት | *በአርብቶ አደር ደረጃ የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 3. | የወአግፐ አበይት ትኩረት መስክ | | | |
| 3.1 | በየደረጃ ባሉ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት ለመተግበር የተጠናቀቁ የጥናት ውጤቶችን ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በመቃኘት ተግባራዊ ማድረግ | * ተጠንተው ለትግበራ የተዘጋጁ የጥናት ውጤቶች ብዛት | * ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ ያደረጉ ወረዳዎች | * የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 3.2 | በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የህዝብ ፍላጎትና ቅሬታ የሚታወቅበት ጥናት በማካሄድ የመልካም አስተዳደር እመርታን በቀጣይነት ማረጋገጥ | ❖ የህዝብ ፍላጎት ቅድመ ትንበያ የተደረገባቸው ወረዳና ቀበሌ ብዛት<br>❖ የተዘጋጀና የተጠናከረ የህዝብ ፍላጎት የጥናት ሰነድ ብዛት<br>❖ የአሰራር ማሻሻያ የተደረገባቸው ወረዳና ቀበሌያት ብዛት | * የተዘረጋ ቀልጣፋ አሰራር | * የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 2. | *የፍትህ ሥርዓት ኘሮግራም ቁልፍ የትኩረት መስክ* | | | |
| 3 | የክልሉን የፍትህ ሥርዓት ለማሻሻልና ከመሠረቱ ለመለወጥ የተወጠኑ ሥራዎችን በማጠናከር የፍትህ አካላቱን ተደራሽነት፣ቀልጣፋነት፣ ፍትሃዊነትና ውጤታማነት ማረጋገጥ ነው፡፡ | | | |
| 3.1 | በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትን በስልጠና ማብቃት ፣ | ➢ የሠለጠኑ የህግ ባለሙያዎች ብዛት<br>➢ ውስጣዊ አደረጃጀቱ የተጠናከረ የህግ ሥልጠና ማዕከል ብዛት<br>➢ በህግ የሰለጠኑ የአርብቶ አደር ባለሙያዎች | ➢ በሥልጠናው የረኩ የህግ ባለሙያዎት ብዛት<br>➢ የሚጠበቅበትን አገልግሎት መስጠት የቻለ የሥልጠና ማዕከል<br>➢ በባለሙያ አቅማቸው የተሟላ የህግ ተቋማት | • በሥልጠና ስኬታማና ውጤታማ የሆኑ የፍትህ ማካላት |
| 3.2 | የኀብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ሥርዓት፣ | ➢ የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ አደጃጀት የተቋቋመላቸው ቀበሌዋች ብዛት<br>➢ በኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ላይ ሥልጠና የወሰዱ አካላት ብዛት | ➢ በሥልጠናው የረኩ ሠልጣኞች ብዛት<br>➢ ኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሥራ ላይ የዋለባቸው ቀበሌዎች ብዛት | • ሰላምና ፀጥታ የተጠበቀለት ህብረተሰብ |
| 3.3 | ህብረተሰቡ የፍትህ ሥርዓቱን የራሱ መሆኑን ተገንዝቦ አጥጋቢ የሆነ ተሰትፎ የሚያደርግበት የአሠራር ሥርዓት | የመሰረታዊ ህጎች ክላሰና ጠውናቶቹ አልቀዉ ረቂቆቹ ተዘጋጅተዉና ደብረዉ እንዲፀድቅ እገዛ የደረገ ህብረተሰብ | የመሠረታዊ ህጎች ክላሰና ጥናት በአስተያየት እንዲዳብር ያደረገ የህብረተሰብ ክፍሎች | በጥናትና በአስተያየት የዳበረ መሠረታዊ ህጎች |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 3.4 | ከመደበኛ ፍርድ ሥርዓት ወጪ አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ መንገዶችን ለመጠቀም የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት | • ከመደበኛ ፍርድ ሥርዓት ወጪ አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ ሥርዓት ታጠቃሚ የሆነ ህብረተሰብ<br>• የሙግት መፍቻ መንገዶችን በመጠቀም ጊዜና ጉልባቱን ሳያባክን ጉዳዩን የጨረሰ ህብረተሰብ<br>• በግጭትና ሙግት መፍቻ ስርዓት አጠቃቀም ሥልጠና የተሰጣቸዉ ቀበሌዎችና የከተማ አስተዳደር | • አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ ሥርኣት በመጠቀም ጉዳያቸዉ ማለቁን የገለፁ ቀበሌያት ብዘት<br>• በአማራጭ የፍርድ ሥርኣት በተሰጣቸዉ ሥልጠና እርካታቸዉን የገለፁ የሠልጠኞች ብዘት<br>• በአቅራቢያቸዉ ሆነዉ ጊዜያቸዉ፣ ጉልበታቸዉ፣ ሳይባክን ዉሳኔ ማግኘታቸዉን የገለፁ ቀበሌያትና ከተማ አስተዳደር | ጊዜያቸዉንና ጉልበታቸዉን በልማት መዋል የቻሉ ቀበሌያትና ከተማ አስተዳደር |
| 3.5 | የፍትህ ሙያተኞች ማሰልጣኞች ማዕከል ከተቋቋመበት ተልዕኮ አንፃር በትክክል ዓለማዉን ማስከቱን ክትትልና ድጋፍ የተደረገበት አሠራር | • በማሰልጠኛ ማዕከሉ ሥልጠና የወሰዱ ዳኞችና አቃቢን ህግ<br>• ማሰልጠኛ ማዕከሉ ተልዕኮዉን ማሳከቱን የገለፁ ባላሙያዎች | • በማዕከሉ ሥልጠና እርካታቸዉን የገለጸ ኅብረተሰብ<br>• ማሰልጠኛ ማዕከሉ ተልኮዉን ማሳከቱን የገለፁ የፍትህ ተቋማት | የፍትህ ሙያተኞች ማበልፀጊያ ማዕከል |
| 3. | የም/አ/ግ/ፕ ቁልፍ የትኩረት መስክ | | | |
| | የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልክ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ | | | |

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክቶሪያል ግቦች | የዕቅድ አፈጻጸም ውጤት አመልካቾች / Output indicators / | የግብ ስኬት አመልካቾች /Outcome indicators/ | የዕቅድ የሚያስከትለው ፋይዳ አመልካቾች / Impact / |
|---|---|---|---|---|
| 1.1 | የመንግሥትና የግል ቴ/ሙያ ተቋማት የሥልጠና መስኮቻቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል | • የተዘጋጀና የጸደቀ አዋጅ<br>• ለለውጥ ሥራዎች የተሰጠ ድጋፍ | • ወጣቱን ወደ ሙያ ስራ ማሰማራት<br>• የሥራ ዕድል መፈጠር | • የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት<br>• ሥራ አጥ መቀነስ |
| 1.2 | የጥራትና ደረጃ ልማትን በቀጣይነት በማጠናከርከ ጥራትና ደረጃው የተስተካከለ አሠራር መዘርጋት | • ደረጃቸውን የጠበቁ የምርትና የአገልግሎት ተkማት ብዛት | • በገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ማሸነፍ መቻል<br>• የተሻለ ገቢ | • የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 1.3 | የግል ተቋማትና የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዲስትሪና የከተማ ልማትንና የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማጠናከር፣ | • ድጋፍ የተደረገላቸውና የበቁ ተkማት ብዛት | • በገበያ ተወዳዳሪ መሆን<br>• የተፋጠነ የኢንዱስትሪ ዕድገት<br>• ወጪ ቆጣቢ የሆነ የከተማ መሠረተ-ልማት | • የተፋጠነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 2 | የም/አ/ግ/ፕ ቁልፍ የትኩረት መስክ | | | |
| | የግል ሴክተሩ ተጨባጭ የኢኮኖሚ ለውጥ በሚያመጡ<br>የእሴት ሠንሠለት (Value Chain)<br>አሠራሮችን እንዲዘረጉ ማስቻል፣ | • የእሴት ሠንሠለት ሥራ የተጀመረባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች | • በገበያ ተወዳዳሪ መሆን መቻል | -የተቀናጀ የኢኮኖሚ ልማት |
| 2.1 | የዩኒቨርሲቲ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲሆን ማገዝ | • የተተገበሩ አዳዲስ የለውጥ ሥራዎች | • ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት<br>• የኢንዱስትሪ ሴክተሩ መደገፍ | ተቋማዊ ለውጥ |

## 5/ የሚጠበቁ ውጤቶች

## 5.1 የሲ/ሰ/ማሻሻያ ኘሮግራም

*በቁልፍ የትኩረት መስክ የሂደቱ የሲ/ሰ/ማ/ፕ/ ግቦችና የሚጠበቁ ውጠቶች*

1/ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት አጠናቀው ሙሉ ትግበራ ላይ ባሉ በሰባት ሴክተሮች የተዘረጋ ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ/BSC/ ሥርዓት

- ☞ በውጤት ተኮር የዕቅድ አፈጻጸም ሥርዓት ላይ የሰለጠኑ የሰባት ሴክተር መ/ቤቶች ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ብዛት
- ☞ በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶች በBPR እና በውጤት ተኮር ዕቅድ አተገባበር ላይ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ

2/ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ወደ ሙከራ ትግበራ በመግባት ላይ ያሉ ሴክተር መ/ቤቶች ወደ ሙሉ ትግበራ ማሸጋገር

- ☞ የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራ ለሚያደርጉ የስራ ሂደቶች የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍና ግምገማ
- ☞ በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የማትጊያ ክፍያ ሥርዓት
- ☞ የማወዳደሪያ ዕውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት
- ☞ ከኃላፊነት በክብር የሚነሱ ተሿሚዎች ጥቅማጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ ሥርዓት

## 5.2 የወረዳ አቅም ግንባታ ኘሮግራምና መልካም አስተዳደር ፓኬጅ

1. በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተጠናከረ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓት መዘርጋት
   - ➢ ከክልል እስከ ቀበሌ የተዘረጋና የተደራጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሰራር ስርዓት
   - ➢ የተዘጋጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ማስፈጸሚያ መመሪያ
   - ➢ የተዘጋጀ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አሰራር ስልጠና ሰነድ
   - ➢ ለዞንና ወረዳ አመራሮች በማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ የተሰጠ ሥልጠና
   - ➢ ለኢንስፔክሽን ቡድን አባላት በኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን ማስፈጸሚያ መመሪያ ላይ የተሰጠ ሥልጠና
   - ➢ በሁሉም ቀበሌና ወረዳ በፓኬጁ መሠረት የተቋቋመና ሥራ የጀመረ የኢንስፔክሽን ቡድን ፣
   - ➢ በሁሉም ቀበሌ የኢንስፔክሽን ቡድን አባላት ወደ ሥራ ለማስገባት የተሰጠ ሥልጠና ፣
   - ➢ ለቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በእንስፔክሽን አሰራርና አደረጃጀት የተሰጠ ስልጠና፣
   - ➢ በክልል ደረጃ የኢንስፔክሽንና ሱፐርቪዥን አገልግሎት የተሰጣቸው አስር ወረዳዎች
   - ➢ የእንስፔክሽን ውጤት፣ግብረ መልስና ሪፖርት

1. በሁሉም የክልሉ የቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲመራ ማድረግና አሣምኖ ማሠራትንና ያልተቋረጠ ተሳትፎን በማጠናከር ምርጥ ስኬቶቻችንን ማስፋፋት

- በፓኬጅ ላይ በተገለፀው መስፈርት መሠረት በሞዴልነት የተመረጡ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች
- የመሪነት ሚና መጫወት እንዲያስችላቸው የተሰጠ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ፣
- የተመረጠ ሞዴል ግለሰብ መንደርና ቀበሌ ፣
- የቀበሌ ምክር ቤት፣የብዙሃን ማህበራት እንዲሁም የባህላዊ ተቋማት ተሳትፍን ለማጎልበት የተሰጠ ምክርና ድጋፍ
- በክልል፣በዞንና ወረዳ ደረጃ የተጠናከረ የምርጥ ተሞክሮ ሰነድ

2. በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከር ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ የተዘረጋ የአሰራርና የአደረጃጀት ስርዓት

- የገጠር ልማት ተግባሮች በቀበሌ ደረጃ ተጣምሮና ተቀናጅቶ ወደ ተግባር የሚወርዱበት የዕቅድ አዘገጃጀትና ሪፖርት አቀራረብ አሠራር፣
- በቀበሌ ደረጃ የተዘረጋ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት የመረጃና የጉዳይ አቀባበል አሠራር
- አራቱ የልማት ኮሚቴዎች በተቀናጀ ሁኔታ የሚሰሩበትን አሰራር በተጠናከረ መንገድ ማስቀጠል
- በቀበሌና ወረዳ ደረጃ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን ተግባራዊ ለማድረግ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ ለሥራ አስኪያጁና ለሚመለከታቸው አካላት የተፈጠረ ግንዛቤ

3. በሁሉም አርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተደርጎ የተቀረፀውን የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ በተሟላ ሁኔታ መተግበር

- በፓኬጅ መሠረት ለቀበሌ አመራሮች የተሰጠ ስልጠና፣
- በፓኬጁ ላይ ለፈጻሚ ሰራተኞችና ለአርብቶ አደሩ ኅብረተሰቡ የተሰጠ ስልጠና፣
- ለአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ማስፈጸሚያ የተዘጋጁ መመሪያዎች
- በተዘጋጁ መመሪያዎችና አሰራሮች ላይ ለአስፈጻሚውና ፈጻሚው የተፈጠረ ግንዛቤ
- የመልካም አስተዳደሩ ፓኬጅ በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን የተሰጠ ድጋፍና ክትትል

4. በየደረጃ ባሉ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት ለመተግበር የተጠናቀቁ የጥናት ውጤቶችን ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ ሃሳብ አንጻር በመቃኘት ተግባራዊ ማድረግ

    - የወረዳ የህግ ማቀፍ፣ ያልተማከለ አስተዳደር ፖሊሲና ስትራቴጂ ዝቅተኛ አገ/አሰጣጥ እስታንዳርድ ፀድቆ የተገበሩ ወረዳ

5. በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የህዝብ ፍላጎትና ቅሬታ የሚታወቅበት አሰራር በመዘርጋት የልማትና የመልካም አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር

- በተመረጡ ወረዳና ቀበሌ የህዝብ ፍላጎትና ቅሬታ ለመቀመር የተካሄደ ቅኝት፣ ውጤትና ግብረ መልስ

## *5.3 የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም*

## የሂደቱ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች

### በቁልፍ የትኩረት መስክ ሴክቶሪያል ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች

I. በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትን በስልጠና ማብቃትና ተቋማቱን በማቴሪያል መደገፍ፣

- ከአርብቶ አደር አካባቢ ተመልምለው የሕግ ትምህርት የጀመሩ 100 የዲኘሎማ ተማሪዎች
- አዲስ ተመልምለው ስልጠና ለሚገቡ 200 የፖሊስ መኮንኖች የተሠጠ ድጋፋዊ ክትትል
- 250 ዲኘሎማና ዲግሪ የተሐድሶ ስልጠና እንዲያኙ ለተደረጉ ዳኞችና አቃቢያን የተሠጠ ድጋፋዊ ክትትል
  - 150 ዲኘሎማና 50 ዲግሪ የወረዳ ዳኞችና አቃቢያን ሕግ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለተሰጠቸዉ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል
  - በክልሉ የፍትሕ ማሠልጠኛና የህግ የምርምር ማዕከል ተቋምና ለፍትሕ ተቋማት አሠራራቸውን ለማሻሻል የተደረገለቸዉ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችና ሌሎች ድጋፍ፣

2. ህብረተሰቡ የፍትህ ሥርዓቱን የራሱ መሆኑን ተገንዝቦ አጥጋቢ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርግበት የአሠራር ሥርዓት
   - የፍርድ ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም በርካታ ፕሮጅክቶች የፋይል አያያዝ ፣ቀልጣፋ የችሎት ሂደት አመዘጋገብ ሥርዓትና ሥልጠና፣ ተዘዋወሪ ችሎት መዘርጋት፣ ቀጠሮ በሰዓታት በትኖ መስጠት፣የባላጉደይ አቤቱታ ማቅራቢያ ፎርሞች፣ የፍርድ ቤት የሥራ አፈፃፀም መለኪያዎች፣በሥራ ላይ ያሉ ዳኞች ሥልጠና ተግባራዊ ያደረጉ የተለያዩ ደረጃ ያለቸዉ ፍርድ ቤቶች፣
   - የመሠረታዊ ህጎች ክለሳ በታቀደዉ መሰረት ጥናቶቹ አልቀዉ ረቂቆቹ ተዘጋጅተዉ ለባላድርሻዎች ወርክሾፖች ቀርበዉ ዳብረዉ በዉሳኔ ሰጪ አካላት እንዲፀድቅ እገዛ ያደረገ የህብረተሰብ ክፍሎች፣
   - እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ ውሣኔ አሠጣጥ ሥርዓት የተደረገ ድጋፍና ክትትል፣
   - በሥነ ምግባር መከታተያና መለያ ሥርዓት የተሐድሶ ሥልጠና በመከታተል ላይ ላሉ ዳኞችና አቃቢያን ሕግ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትል፣

- የፍ/ቤቶችን ተደራሽነት ቀጣይነት ለህብረተሰቡ ተግበራዊነቱን ክትትልና ድጋፍ ያደረጉ ባላሙያዎች፣
- የተፈጠነ እና ቀልጠፋ ፍትህ ለተገልጋዩ ከመስጠት አንፃር እስከ ሁለት ወር ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ፍትህ የሰጡ ፍርድ ቤቶችና ፍትህ ተቋማት፣
- የፍርድ ጥራትን ከመጠበቅ አንፃር በይግባኝ የሚሻሩ ጉዳዮችን 99% እንዲቀንስ በተዘረጋ ሥርዓት አፈፃፀማቸዉን ያሻሻሉ የተለያዩ ዳረጃ ፍርድ ቤቶች፣
- የተገልጋዮች ጊዜ ፣ጉልባትና ወጪ በመቆጠብ ወጪ ቆጣቢና ተደራሽ የሆነ ፍትህ የሰጡ በየደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች፣
- የሰዎችን ሰብአዊ ክብር የሚያስጠብቅ አያያዝ እንዲኖር ያደረጉ ማረሚያ ቤቶች፣

3. ኅብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅና ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍትህ አካላት ጋር በመቀናጀት የተዘረጋ ሥርዓት፣

- በክልሉ በከተማና ገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ የተቋቋሙ ቀበሌዎች፣
- የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት ለማስፋፋት የሌሎች ክልሎች ተሞክሮ በሥራ ሂደት መጠቀማቸዉን ድገፋዊ ክትትል፣
- ሙያዊ አቅም ለመገንባት ከሌሎች አሳልጣኝ ተቋማት ጋር ስምምነት በማድረግ ሥልጠና የወሰዱ የፖሊስ መኮንኖች፣

4. ከመደበኛ የፍርድ ሥርዓት ወጪ አማራጭ የግጭትና የሙግት መፍቻ መንገዶችን ለመጠቀም የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት

- አማራጭ የሙግት መፍቻ ወይም የግጭት ማስወገጃ ሥርዓት ተግበራዊ ያደረጉ ቀበሌያት፣
- አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌሎች ዉሳኔ ሰጪ አካላትን እንዲጠናከር ያደረጉ ቀበሌና ከተማ አስተዳደር፣
- ወጠቶች ከመደበኛ የፍርድ ሥርዓት ዉጪ ማረም የቻሉ ማረሚያ ቤቶች፣
- በህዝቦች መካከል ግጭቶች የሚቆሙበትንና የሚቀሩበትን መንገድ በማጥናት የተቀየሰ የአፈፃፀም ስልት፣

## *5.4 የም/አቅም ግንባታ ማሻሻያ ኘሮግራም*

### የፕሮግራሙ ግቦችና የማጠበቁ ውጤቶች

1. የመንግሥትና የግል የቴ/ሙ/ያ ተቋማትን ማጠናከርና የሥልጠና መስኮቻቸውን አጠናክሮ እንዲቀጥሉ ማድረግ፣

   - የክልሉ የቴ/ሙ/ት/ሥ/አዋጅ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል መደገፍና በአዋጁ መሠረት የተቋቋመ ሥራ የጀመረ ቦርድ ካውንስል ፣
   - የተዘጋጀ የሙያ ደረጃ (OCCUPATIONAL STANDARD DEVELOPMENT)
   - የቴ/ሙ/ት/ መምህራን የሙያ ብቃት ምዘና የወሰዱ መምህራን ብዛት
   - በቴ/ሙ/ት/ሥ/ የለውጥ ሥራዎች ላይ የተሰጠ ክትትልና ድጋፍ፣
   - በአዲሱ የአሠለጣጠን ሥርዓት መሠረት የተዘጋጀ ሥርዓተ-ትምህርት
   - የቴ/ሙ/ት/ መምህራን በ ኤ.ቢ.ሲ ደረጃ የተሰጠ ሥልጠና፣
   - በሁሉም የሙያ መስኮች የተሰጠ የልህቀት ምዘና፣

2. ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አሰራርን በቀጣይነት በማጠናከር የተቋማትን አቅም ማጎልበት

   - የክህሎት ውድድር የተካሄደባቸው ተkማትና የሙያ መስኮች
   - በጥቃቅን አነስተኛ ተkማት ለተደራጁና በሥራ ላይ ላሉ የተሰጠ ድጋፍ፣
   - ለደረጃ አንድና ሁለት የሙያ መስክ የተዘጋጀ ሙያዊ ደረጃ መስፈርት ላይ የተደረገ ድጋፍ፣

3. የግል ተቋማት፣ የአነስተኛና ጥቃቅን እንዱስትሪ እና የከተማ ልማትን ማጠናከር ፣

- በእሴት ሠንሠለት አሠራር ዙሪያ የተሠጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና
- በቅንጅት የእሴት ሠንሰለት የተገበሩ ተቋማት፣
- በክልሉ አዳዲስ ተጨማሪ የተለዩ/የተመረጡ/ የእሴት ሠንሠለት ሥራዎች፣
- የትብብር ሥልጠና መስጠት የቻሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ፣
- በተሠማሩበት የኢኮኖሚ መስክ ውጤታማ ለሆኑት የግል ተቋማት የተደረገ ቴክኒካል ድጋፍ፣
- የጥርብ ድንጋይ ንጣፍ ሥራ በራሳቸው ባጀት ሥራ የጀመሩ የሪፎርም ከተሞች፣

4. የዩኒቨርሲቲ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ …
   - በዩኒቨርሲቲ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሥራዎች ላይ የተሰጠ ክትትልና ድጋፍ፣
   - በዩኒቨርሲቲና በኢንዱስትሪ የተፈጠረ ቅንጅታዊ አሠራር

## 5.2 በአበይት ትኩረት መስክ የፕሮግራም ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች

1. በሥልጠና ተቋማት የሚሠጠው ሥልጠና የግል የሥራ ፈጠራን በማበረታታት ተፈላጊ የሙያ መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ በሁሉም በመንግሥትና በግል ተቋማት ውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት የሚያስችል የተዘረጋ ሥርዓት፣

   - 70% የተሟላ የተግባር ሥልጠና መስጠት የቻሉ የማስልጠኛ ተቋማት፣
   - ገበያ ላይ ተፈላጊ በሆኑ የሙያ መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ ሙሉ ለሙሉ ሥልጠና መስጠት የጀመሩ ተቋማት፣
   - ሠልጥነውና ተደራጅተው ወደ ግል ሥራ የገቡ…. ማህበራት፣

❖ የእሴት ሠንሠለት (Value Chain) አሠራርን በማስተሳሰር በሁሉም ባለ ድርሻ አካላት እንደ ሥርዓት መትከል፣

▪ በእርሻ ምርት ውጤቶች ላይ የእሴት ሠንሠለት አሠራር ሥርዓትን የተገበሩ ተቋማት

## 9. አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች

### 9.1 አዎንታዊ ታሳቢዎች

- በ 2002 በጀት ዓመት ጀምሮ /PSCAP TWO/ ፒስካፕ ለቀጣይ አምስት አመት የሚቀጥል መሆኑ
- የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻልና የአመለካከት ለውጥ መኖር
- የሠራተኞች ግንዛቤ መዳበርና በግቦች ላይ የጋራ መግባባት መፈጠር
- የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ የመጀመሪያ ዙር በተሳካ መልኩ ወደ ሙሉ ትግበራ መግባቱ
- በአለም ባንክ በኩል ያሉ አሰራሮች መሻሻሉ
- የተጠያቂነትና የግልጸኝነት አሰራር እየሰፈነ መምጣቱ

### 9.2 አሉታዊ ታሳቢዎች

- ብድርና ዕርዳታ በጀት መዘግየትና የዶላር ምንዛሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ መምጣቱ
- የሴክተሩ የመደበኛ በጀት ማነስ
- ተሽከርካሪ ተሟልቶ አለመገኘት
- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ በደረጃው የሚገኙ አመራሮች ግንዛቤ ውሱንነትና ቁርጠኝነት አለመኖር
- የአመራር አካላትና ባለሙያዎች በ□□□□ መቀያየርና መልቀቅ
- የሰው ሀይል በሚፈለገው መጠን አለመሟላት
- የተጠናከረ የሕዝብ ግብኙነትና የመረጃ ሥርዓት ያለመዳበር
- የፒስካፕ በጀት አጠቃቀም በዕቅድ ላይ አለመመስረትና በደራሽ ሥራ ላይ ማተኮር

## 10. የክትትል፣ሪፖርት እና ግምገማ ስርዓት

በአወንታዊ ታሳቢነት ተለይተው የተቀመጡ ዋና ዋና ጉዳዩች እንደተጠበቁ ሆኑ ሴክተሩ ዕቅዱን በተሟላ ሁኔታ ለመፈጸምና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ብሎም ተልዕኮዉን ለመወጣት

ነው። ይህም ዕቅዱን በጊዜ ገደብ ለመስራት ከታቀደው ምን ያህሉን በምን ያህል ወጪና በምን ዓይነት ጥራት እንደተተገበረ ካጋጠሙት መሰናክሎችና መልካም ገጠመኞች አንጻር የሚገመገምበት ነው።

በአጠቃላይ የክትትልና የግምገማው ስርዓት በተከታታይ የሚከናወን ሆኖ የሚመለከታቸውን አከላት በተሟላ ሁኔታ ያሳተፈና የመረጃው አሰባሰብ ከተለያዩ አከላት ተወስዶ የተነጻጸረና በተገቢው ሁኔታ የተጣራ መሆን ይገባዋል። በተጨማሪ ክትትሉም ሆነ ግምገማው ሲካሄድ ከተዘረዘሩት የውጤት፣ ስኬትና ፋይዳ/ለውጥ አመልካቾች (output, outcome and impact indicators) ለግቡ መፈጸም ከሚያደርጉት አስተዋጽዖ አንጻር መሆን ይኖርበ□ል።